የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን
ዓለም አቀፍ ማሕበር
WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF E.O.T. CHURCH
4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

# ታ ላ ቅ ጉ ባ ኤ

## 2ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር ጉባኤ፤

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

1ኛ/ የጉባኤው ዓላማ፤

የጉባኤው መሠረታዊ ዓላማ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከውስጥና ከውጭ የተደቀኑባትን ከባድ ችግሮች በጥልቀት ለመመርመርና ተገቢ የሆኑ መፍትሔዎችን ለመጠቆም እንዲሁም ምእመናን፤ ከአባቶች ጋር በቅርብ በመተባበር፤ ተጨባጭ እርምጃዎችን በሕብረት በመውሰድ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ፍቅር፤ ሰላም፤ አንድነት፤ እድገትና መስፋፋት የሚያስገኙ ሐሳቦችን በተቀናጀና ውጤታማ በሚሆን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

2ኛ/ የጉባኤው ዝግጅት፤

ጉባኤው የሚከናወነው መስከረም 19 እና 20 ቀኖች 2004 ዓ/ም (September 30 and October 1, 2011)፤ ር እሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ ዋሺንግተን ዲ.ሲ. ሲሆን አዘጋጆቹም ደብሩና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር ናቸው። ለዚሁም የዝግጅት ተግባር ከሁለቱ ድርጅቶችና ከሌሎችም ደብሮች የተውጣጣ ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ሥራውን እያከናወነ ነው።

3ኛ/ የጉባኤው አቅራቢዎችና ተሳታፊዎች፤

ጉባኤው በሚያተኩርባቸው አርእስቶች ላይ ጥናታዊ ጽሑፍና ገለጻ የሚያቀርቡት በጥንቃቄ የሚመረጡ ምሑራን አባቶችና ምእመናን ይሆናሉ። የጉባኤው ፕሮግራምና የአቅራቢዎች ስም ዝርዝር በቅርቡ ይገለጻል። በጉባኤው፤ ካሕናትም ሆኑ ምእመናን ሊሳተፉ ይችላሉ።

4ኛ/ ጉባኤው የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች፤

ጉባኤው የሚወያይባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፤

4.1 ቤተ ክርስቲያናችን በዶግማዋና በጥንታዊነቷ የታወቀች ሆኖ ሳለ፤ ባሁኑ ዘመን፤ በፖለቲካ፤ በዘር፤ በሥልጣንና በጥቅም አሳዛኝ ዓለማዊ ምክንያቶች እየተናወጠች በመሆኑ፤ እነዚህ ከባድ ችግሮች ተወግደው፤ አንድነት፤ ፍቅር፤ ሰላምና የተፋጠነ ልማት እንድታገኝ ስለ ማድረግ፤

4.2 የቤተ ክርስቲያናችን ትምሕርትና ስብከት ተጠናክሮ በዓለም በሙሉ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመጠቀም ጭምር ስለሚስፋፋበት፤ እንዲሁም ወጣቱ ትውልድ ስለ ሃይማኖቱ ጥልቅ እውቀትና እምነት እንዲኖረው ስለ ማድረግ፤

4.3 በያሉበት ስለሚገኙት የቤተ ክርስቲያናችን ደብሮችና ገዳሞች፤ ኢየሩሳሌም ገዳማችን ጭምር፤ እንዲሁም የአብነት ትምሕርት ቤቶች ስለሚያስፈልጋቸው እርዳታና ድጋፍ፤

4.4 ምእመናን ለቤተ ክርስቲያናችን አጥጋቢ ውጤት እንዲያስገኙ ስለሚያስችል ስልትና አደረጃጀት፤

4.5 በቤተ ክርስቲያናችን ላይ በተነሳሱት ተቃዋሚዎች የተቃጣው ጥቃት ስለሚወገድበት ስልት፤

5ኛ/ <u>ለጉባኤው ከንውን ስለሚያስፈልግ ድጋፍ፤</u>

ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ ተከናውኖ ለቤተ ክርስቲያናችን የዘለቄታ ጥቅም እንዲገኝ ለማድረግ፤ ደብሮችና ምእመናን እርዳታቸውን በሚቀጥለው አድራሻ እንዲያበረክቱ በትሕትና ይጠየቃሉ፤

World Association of Parishioners of E.O.T. Church
Bank: Wells Fargo
Account No: 9167531723
Routing No: 111900659
Bank Address: 13050 Coit Road, Dallas, TX 75240, USA

6ኛ/ <u>ስለ ዓለም አቀፍ የምእመናን ማሕበር፤</u>

ማሕበሩ የተቋቋመው፤ በ2000 ዓ/ም ሲሆን፤ ዳላስ በሚገኘው ደብረ-ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በ1999 ዓ/ም በተከናወነው ዓለም-አቀፍ የምእመናን ጉባኤ በተወሰነው መሠረት ነው። ማሕበሩ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም፤ ካከናወናቸው ተግባሮች ጥቂቶቹ፤ በአባቶች መሀል የተከሰተው አሳዛኝ መከፋፈልና መወጋገዝ እንዲወገድ ማሳሰብ፤ ኢየሩሳሌም የሚገኘው ታሪካዊ ገዳማችን እንዲጠገን ለእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የአቤቱታ ደብዳቤ ማስፈረም፤ የአብነት ትምሕርት ቤቶች ድጋፍ እንዲያገኙ ማበረታታት፤ እንዲሁም በአጠቃላይ፤ የቤተ ክርስቲያናችን ስልት፤ ፕሮግራም፤ አወቃቀር፤ ትምሕርትና ስብከት እንዲሻሻል ጠቃሚ ሐሳቦች በማቅረብ፤ ወዘተ. የፈጸማቸው ጥረቶች ይገኙበታል። ስለ ማሕበሩ ዓላማና ተግባሮች ዝርዝር ግንዛቤ ለማግኘት፤ www.eotcipc.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ መመልከት ይቻላል።

ስለ ጉባኤው ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ፤ የአዘጋጅ ኮሚቲውን ሊቀመንበር፤ ዶር. አክሊሉ ሐብቴን በቴሌ/ቁ (301)564 9192፤ ጸሓፊውን፤ አቶ ታደሰ ሙላትን በቴሌ/ቁ (243)423 8841 ወይም በtadskmariam@yahoo.com፤ እንዲሁም ከማሕበሩ አመራር አባሎች፤ በአድራሻችን ከተመለከተው በተጨማሪ፤ ቀኛዝማች/ዶር. ሰሎሞን አበበን፤ በቴሌ ቁ (214)697 8928 ወይም በthe_negus@yahoo.com; አቶ ኢዮኤል ነጋን በቴሌ ቁ (469)855 8488 ወይም በeyoelnega@yahoo.com; አቶ ብንያም ሙሉጌታን በቴሌ/ቁ (650)906 8012 ወይም በbmulugeta1020@gmail.com፤ እና ዶር. ወ/አማኑኤል ፈለቀን በ(507)252 1376 ወይም በamanuelfeleke@gmail.com መጠየቅ ይቻላል።

---

ቸሩና ኃያሉ የኢዮጵያ አምላክ፤ ሁልጊዜም በሚመለከባት፤ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችን፤ ፍቅር፤ ሰላም፤ አንድነትና እድገቷ ተጠናክሮ እምነቷም በዓለም በሙሉ እንዲሰፍን ለማድረግ ታሪካዊና ውጤታማ ጉባኤ እንድናከናውን ይርዳን። አሜን።